# ሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና ሰብአዊ አገልግሎቶች ክፍል
# ኮቪድ የኪራይ ፋታ ፕሮግራም – ደረጃ 2

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የጤና እና የሰብኣዊ አገልግሎቶች ክፍል (ዲኤችኤችኤስ) የሚያቀርበው የአጭር ጊዜ የኪራይ ድጋፍ ብቁ ለሆኑ በ ኮቪድ-19 ወረርሽኝ ምክኒያት ባጡት ገንዘብ የተነሳ ኪራይ መክፈል ላቃታቸው ቤተሰቦች ነው። ድጎማዎቹ ሲኖሩ፣ ፕሮግራሙ የሚያቀርበው እስከ $4,000 ለኪራይ ፋታ ለብቁ ቤተሰቦች ሲሆን ይህም ላልከፈሉት ኪራይ እና ለወደፊቱ ወራት ኪራይ ለመሸፈን ሊውል ይችላል። ፕሮግራሙ የሚደጎመው በ $20 ሚሊዮን የተጨማሪ ምደባ ለዲኤችኤችኤስ ሲሆን ይህም በወረርሽኙ ለተጎዱ ተከራዮች ለማገዝ ነው።

ለፕሮግራሙ ደረጃ 2፣ ዲኤችኤችኤስ ያጎለበተው የቤት አልባ መከላከል ማውጫ ሲሆን ይህም በኮቪድ-19 ማመልከቻዎች ቅደም ተከተላቸው የሚወሰነው በ ኮቪድ ተጽእኖ ቦታዎች፣ ከመጀመሪያው "ከባድ ተጽእኖ" ሰፈሮች ውጭ ላሉ ቤተሰቦች (ካርታ የሚገኘው በ bit.ly/mc-hpi-map) በተጠባባቂነት ተይዘው ክፍት ቦታ ሲኖር ይጠራሉ። ይህም የሚያስችለው ፕሮግራሙ ፍትሓማነት እንደሚጠቀም፣ የቀለም ማህበረሰቦች በ ኮቪድ በእጅጉ የተጎዱ ስለሆኑ፣ በብዛት ቤትአልባነት ስለሚያጋጥማቸው፣ እናም ከቤት ለመባረር የበለጠ ተጋላጭ እንደሆኑ ስለምንረዳ ነው።

የሞንተጎመሪ ነዋሪዎች ሆነው ብቁ ነን ብለው የሚያስቡ ሁሉ እንዲያመለክቱ እናበረታታለን **አሁን ያመልክቱ!**
https://seam.ly/WA2HNQO2

**ኪራዬን ለመክፈል ቸግሮኛል። እርዳታ አለ?**
ኪራይ መክፈል ካቆሙ፣ እርዳታ ሊኖር የሚችለው በዲኤችኤችኤስ  የመኖሪያ ቤት ማረጋጊያ አገልግሎቶች በኩል ነው። እባከዎትን የኦንላይን ማመልከቻውን ከላይ ባለው ሊንክ በኩል ይሙሉ፣ በዚህ ይደውሉ 311 (240-777-0311) ወይም የአገልግሎት ጥያቄ ይሙሉ። የጉዳይ ሰራተኛ ደውሎ ብቁነትዎን ይገመግማል።

**ለ ኮቪድ የኪራይ ፋታ ደረጃ 2 ፕሮግራም ብቁ ማነው?**

ሙሉ ብቁነት የሚወሰነው በመኖሪያ ቤት ሰራተኛ ነው። መጠይቆች የሚያጠቃልሉት፥

- ቤተሰቦች በ 60% ወይም ከዛ በታች ኤኤምአይ፣ በባለፉት 30 ቀናት ገቢያቸው ላይ ተመስርቶ ሊኖራቸው ይገባል (ከስር ያለውን ሰንጠረዥ ይመልከቱ)።
- ቤተሰቦች የገቢያቸውን 50% ቢያንስ በኪራይ ላይ እየከፈሉ መሆን አለበት።
- የገቢ እጦቱ ከ ኮቪድ-19 ጋር መዛመድ አለበት።
- ቤተሰቦች ከኪራይ ክፍያቸው ቢያንስ አንድ ወር ወደሁዋላ መሆን አለባቸው።
- ለስራ አጥነት ጥቅማ ጥቅሞች አመልክተው መሆን አለበት (ብቁ ከሆኑ)።
- ቢያንስ ከፌብሩዋሪ 2020 ጀምሮ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ መሆን አለበት።
- ቤተሰቦች የተለመደ ወይም ያልተለመደ የሊዝ ስምምነት ሊኖራቸው ይችላል።

| *የቤተሰብ ብዛት* | *ትልቁ አመታዊ የቤተሰብ ገቢ* **60% ኤኤምአይ** | *ትልቁ ወርሃዊ የቤተሰብ ገቢ* **60% ኤኤምአይ** |
|---|---|---|
| 1 | $51,000 | $4,250 |
| 2 | $58,260 | $4,855 |
| 3 | $65,529 | $5,461 |
| 4 | $72,780 | $6,065 |
| 5 | $78,660 | $6,555 |
| 6 | $84,480 | $7,040 |
| 7 | $90,300 | $7,525 |
| 8 | $96,120 | $8,010 |

**ከጓደኛ ጋር የቤቱን የተወሰነ ወጪዎች ለመክፈል ስምምነት አለኝ፣ ነገር ግን የራሴ ሊዝ የለኝም። ለእርዳታ ብቁ ነኝን?**
አዎ፣ ያልተለመደ ሊዝ ቢኖርዎም እንኳን ለእርዳታ ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ።

**ምን ያህል ማቅረብ ይችላሉ?**
የተለመደ ሊዝ ያላቸው ብቁ ቤተሰቦች $4,000 ይቀበላሉ። ያልተለመደ የኪራይ ስምምነት ያላቸው ብቁ ቤተሰቦች በወርሃዊ የኪራይ ወጪያቸው ላይ ተመስርቶ እስከ $4,000 የሚደርስ የኪራይ እርዳታ ሊቀበሉ ይችላሉ።

**ገንዘቡን የምቀበለው በቀጥታ ነውን?**
ባብዛኛው ሁኔታዎች፣ ድጎማው በቀጥታ የሚሄደው ለቤቱ ባለቤት ሲሆን የኪራይ ወጪዎን ለመሸፈን ይውላል። በስማቸው ሊዝ ለሌላቸው እና ያልተለመደ የኪራይ ውል ላላቸው ቤተሰቦች፣ ድጎማው ለአከራዩ በቀጥታ ሊቀርብ ይችላል።

**እንዴት ማመልከት እችላለሁ?**

አማራጭ 1 – ኦንላይን ማመልከት፥ ጥያቄዎን በቀጥታ ወደ ዲኤችኤችኤስ ድረገጽ ላይ ማመልከት ይችላሉ። ከመላክዎ በፊት ጥያቄዎችን እንዲመልሱ እና የተወሰኑ ዶክመንቶች እንዲጭኑ ይጠየቃሉ። በተጨማሪም ዶክመንቶችን በዚህ አድራሻ ኢሜይል ማድረግ ይችላሉ HSS@montgomerycountymd.gov.

አማራጭ 2 - 311፥ እርዳታ ለመጠየቅ፣ እባክዎትን የ 311 አገልግሎት መጠይቅ ይፍጠሩ ወይም በ 311 (240-777-0311) ይደውሉ። መረጃ፣ የኢሜይል አድራሻ (ካለ) እንዲያቀርቡ ይጠየቃሉ። በአገልግሎት መጠይቅ ማጠቃለያ ሳጥን፣ እባክዎትን የአዋቂዎች እና ህጻናትን ቁጥር፣ የወርሃዊ ኪራይ፣ እና የአሁን የቤተሰብ ገቢን ይደምሩ። እባክዎትን የመገኛ ምርጫዎን (ኢሜይል ወይም ስልክ) ይዘርዝሩ፤ እንዲሁም ማንኛውም ተጨማሪ የመገኛ መረጃ በ "አጭር ገለጻ" ርእስ ስር ያቅርቡ። የተከፈተ የአገልግሎት መጠይቅ ያላቸው ደዋዮች በፕሮግራም ሰራተኛ ማመልከቻ እንዲሞሉ ስለሚነገራቸው፣ ተጨማሪ መጠይቅ መላክ አይኖርባቸውም። እባክዎትን የአገልግሎት መጠይቅ ቁጥሩን በመያዝ ከፕሮግራሙ እስኪጠሩ ይጠብቁ።

አማራጭ 3 – የመዳረስ ሰራተኛ፥ ዲኤችኤችኤስ የመዳረስ ሰራተኞች ሰዎችን በአካል በመጎብኘት ማመልከቻቸውን ለማገዝ የተመረጡ ቦታዎችን ያዳርሳል። እነዚህ ክንውኖች በተሳታፊ ቦታዎች ላይ በቅድሚያ ይተዋወቃሉ።

**ምን አይነት ዶክመንቶች እፈልጋለሁ?**

- **የ ኮቪድ-19 ተጽእኖ የራስ ማረጋገጫ፥** የገቢ እጦት እንዳጋጠምዎት ራስዎ እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ (ለምሳሌ፣ ከስራ መቀነስ፣ መከልከል፣ ወይም ከስራ መባረር) ወይም በ ኮቪድ-19 የተነሳ ያልተጠበቀ የህክምና፣ የልጅ እንክብካቤ፣ ወይም የዩቲሊት ወጪዎች መጨመር።

- **የገቢ ማረጋገጫ፥** የሚጠየቁት ዶክመንቶች እንዲያቀርቡ እና ወይም ጠቅላላ የቤተሰብ ገቢዎ በቤተሰብ ብዛት ላይ ከተመሰረተው የፕሮግራሙ ገደብ እንደማይበልጥ ራስዎ እንዲያረጋግጡ ነው።
- **የነዋሪነት ማረጋገጫ፥** ቢያንስ ከፌብሩዋሪ 2020 ጀምሮ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ነዋሪ እንደሆኑ ራስዎ እንዲያረጋግጡ ይጠየቃሉ።
- **የአከራይ ዶክመንቶች፥** ከአከራይዎ የወርሃዊ የኪራይ ወጪ የሚያሳይ  እንዲሁም ኪራይዎን ቢያንስ ለአንድ ወር እንዳልከፈሉ የሚያሳይ ዶክመንት መላክ አለብዎት።
- **ፎቶ መታወቂያ፥** የመንጃ ፈቃድ ኮፒ፣ ፎቶ መታወቂያ፣ ወይም ፓስፖርት ለያንዳንዱ አዋቂ አባል።
- **የስራ አጥ ጥቅማ ጥቅሞች፥** ለስራ አጥ ጥቅማ ጥቅሞች ብቁ የሆኑ ቤተሰቦች ማመልከታቸውን ወይም ለማመልከት መሞከራቸውን ማረጋገጥ አለባቸው።

**እንደ ማመልከቻው አካል የሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥር ይጠይቃሉ?**
ሶሻል ሴኩሪቲ ቁጥሮች አይጠየቁም። የፎቶ መታወቂያ ይጠየቃል።

**ከቀጣሪ ደብዳቤ የለኝም፣ ራሴን የማሰራ ነኝ፣ ወይም መደበኛ የስራ ሰኣታት የለኝም። ገቢዬን ለማረጋገጥ ምን ላድርግ?**
ይህንን ቅጽ በመጠቀም የራስ ማረጋገጥ ለመሙላት ይችላሉ።

**ይህንን እርዳታ ለመጠየቅ የመጨረሻው ቀን መቼ ነው?**
በቻሉት ፍጥነት እንዲያመለክቱ በእጅጉ እናበረታታለን፤ ድጎማው የተወሰነ ቢሆንም ማመልከቻውን የመላኪያ ቁርጥ ያለ የመጨረሻ ቀን በዚህ ወቅት የለም።

**በታለሙት  "ከባድ ጫና" ሰፈሮች  ከተባሉት ውስጥ በአንዱም ካልኖርኩስ?**
የ ኮቪድ ኪራይ ፋታ ፕሮግራም – ደረጃ 2 ቅድሚያ የሚሰጠው ቤተሰቦች የተከራዩት በ "ከባድ ጫና" ሰፈሮች ከሆነ ወይም አሁን ቤት አልባ ከሆኑ ነው። የተፈቀደላቸው ብቁ ቤተሰቦች፣ ነገር ግን በታለሙት "ኪራይ ፋታ" ሰፈሮች የማይኖሩት የፕሮግራም አቅም እንደፈቀደ ጥሪ ይደረግለታል።

**ወደ 311 ደውዬ ከዲኤችኤችኤስ  ኮቪድ  ኪራይ ፋታ ፕሮግራም እርዳታ በዚህ አመት ቀደም ብዬ ጠይቄያለሁ፣ ነገር ግን በተጠባባቂ ላይ ተቀምጬ እርዳታ እስካሁን አላገኘሁም። በተጠባባቂ ዝርዝር ላይ እንዳለሁ እንዴት አውቃለሁ? እናስ በድጋሚ ማመልከት አለብኝ?**
አይ፣ በተጠባባቂ ላይ ቢኖሩም እንኳን በድጋሚ ማመልከት የለብዎትም። የመኖሪያ ቤት ማረጋጊያ ሰራተኛ በ 311 ለደወሉት ሁሉ ጥሪ አድርጎ ማመልከቻውን ለመሙላት ድጋፍ ያደርግልዎታል።

**ከመጀመሪያው ደረጃ የዲኤችኤችኤስ ኮቪድ ኪራይ ፋታ ፕሮግራም ወይም ከሌላ የኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም በዚህ አመት ቀደም ብሎ የእርዳታ ድጎማ ተቀብዬአለሁ። ለተጨማሪ ድጎማዎች በድጋሚ ማመልከት እችላለሁ?**
በዲኤችኤችኤስ ኮቪድ ኪራይ ፋታ ፕሮግራም  – ደረጃ 1 በዚህ አመት ቀደም ብሎ ወይም በስቴት የተደገፈ የመኖሪያ ቤት ፋታ ፕሮግራም በኩል እርዳታ ተቀብለው ከሆነ፣ ድጎማዎችን ለመቀበል ብቁ <u>አይደሉም </u>።

ለሁሉም ሌሎች የዲኤችኤችኤስ ኪራይ እርዳታ ፕሮግራሞች፣ የተለመደው 12-ወራት የጥቅማ ጥቅም ገደብ በዚህ የህዝብ ጤና ድንገተኛ ወረርሽኝ ወቅት ገደቡ ተነስቶዋል። ሌሎቹን የብቁነት መጠይቆች ካሙዋሉ፣ ጥቅማ ጥቅም አሁንም ሊያገኙ ይችላሉ። በተጨማሪም፣ በመኖሪያ ቤቶች እድሎች ኮሚሽን (ኤችኦሲ) ኮቪድ የኪራይ ድጋፍ ፕሮግራም በኩል እርዳታ ከተቀበሉ፣ ጥቅማ ጥቅም  ሊያገኙ ይችላሉ።

**ለኮቪድ-19 ኪራይ ፋታ ፕሮግራም በኤችኦሲ በኩል በኦገስት አመልክቼ ነበር። ይህ ፕሮግራም አንድ አይነት ነውን?**
አይ፣ የዲኤችኤችኤስ ኮቪድ-19 ኪራይ ፋታ ፕሮግራም የተለየ እና ከኤችኦሲ ኮቪድ-19 የኪራይ እርዳታ ፕሮግራም የተለየ የብቁነት መመሪያዎች አሉት። ይህ ፕሮግራም የሚተዳደረው በዲኤችኤችኤስ የመኖሪያ ቤት ማረጋጊያ አገልግሎቶች በኩል ነው። የ ኮቪድ-19 ኪራይ እርዳታ ፕሮግራም የሚተዳደረው በመኖሪያ ቤት እድሎች ኮሚሽን ሲሆን የራሱ የብቁነት መመሪያዎች አሉት። ቤተሰቦች ለሁለቱም ፕሮግራሞች ሊያመለክቱ ይችላሉ። ለ ኮቪድ-19 ኪራይ ፋታ ፕሮግራም ብቁ ልሆን

እችላለሁ ብለው ካሰቡ፣ ከላይ በተጠቀሰው ብቁነት መሰረት፣ የኦንላይን ማመልከቻውን ይሙሉ፣ ወደ 311 ይደውሉ፣ ወይም የኦንላይን የአገልግሎት መጠይቁን ይሙሉ።

**ለ ኮቪድ-19 የኪራይ ፋታ ፕሮግራም ብቁነት እንደ ገቢ የሚቆጠረው ምንድን ነው?**
ፕሮግራሙ የሚመለከተው ካለፉት 30 ቀናት ያለውን ማንኛውም ገቢ ነው። ይህ የሚያጠቃልለው፣ ነገር ግን የማይወሰነው፣ በደሞዞች፣ ሶሻል ሴኩሪቲ፣ የጥሬ ገንዘብ ድጋፍ፣ የስራ አጥ (በሂደት ያለ ወይም አሁን እየተቀበለ ያለ)።

**ይህንን ገንዘብ በ 2020 ግብር ላይ ሪፓርት ማድረግ አለብኝ?**
አይ፣ በአብዛኛው ድጎማው በቀጥታ የሚሄደው ወደ ቤት ባለንብረቱ ሲሆን ወደ ኪራይ ክፍያው ሂሳብ ይገባል።

**ይህንን እርዳታ መቀበል እንደ የህዝብ ውዝፍ ይቆጠራልን?**
ዲኤችኤችኤስ በህዝብ ውዝፍ ላይ ህጋዊ ባለስልጣን አይደለም። ስጋት ካለዎት የሚከተሉትን ህጋዊ መረጃዎች እንዲያገኙ እናበረታታለን፥

- የስደተኛ ቤተሰቦችን መጠበቅ
- ጊልክራይስት ማእከል
- ሜሪላንድ የጤና ግንኙነት
- አንድ አገር ኤኤፒአይ  ኤዥያን አሜሪካን እና ፓሲፊክ አይላንደር (አዘውትረው የሚጠየቁ ጥያቄዎች በስፓኒሽ እና በብዙ የኤዥያ ቋንቋዎች)
- ፍትሕ በእርጅና

**እስካሁን ኪራዬን መክፈል ችዬ ነበር፣ ሆኖም ለሚቀጥለው ወር ለመክፈል የምችል አይመስለኝም፤ እርዳታ ማግኘት እችላለሁ?**
ያለ መታደል ሆኖ፣ ይህ ፕሮግራም የሚረዳው ኪራይ መክፈል ላቆሙ ብቻ ነው። እራስዎን በዚህ ሁኔታ ላይ ካገኙ፣ እባክዎትን በዚህ ጊዜ ላይ ደግመው ይደውሉ።

**ይህንን ገንዘብ መልሼ መክፈል ይኖርብኛልን?**
አይ፣ ይህ ብድር አይደለም። ይህንን ለካውንቲው መልሰው መክፈል አይኖርብዎትም።

**አከራዬ ያለብኝን ሁሉ በሙሉ መክፈል ካልቻልኩ አሁኑኑ እንድለቅ ነግሮኛል። የት ነው መሄድ ያለብኝ?**
የፍርድ ቤት ትእዛዝ ያለው ሸሪፍ ብቻ ነው እርስዎን ማባረር የሚችለው። እባክዎትን ወደ አከራይ ተከራይ ጉዳዮች በ 240-777-0311 በማናገር እንዲሁም የፖሊስ ክፍል ድንገተኛ ያልሆነ መስመር በ 301-279-8000 ያናግሩ። ተጨማሪ መረጃ የሚገኘው በመኖሪያ ቤቶች እና ማህበረሰብ ጉዳዮች (ዲኤችሲኤ) ኮቪድ-19 ድረገጽ ላይ ይገኛል።

**ለየመባረር ችሎት ስሞታ የፍርድ ቤት መጥሪያ አለኝ፣ ምን ላድርግ?**
ከኮቪድ ጋር የተገናኘ የመባረር መዘግየት ብቁ ሊሆኑ ስለሚችሉ በፍርድ ቤት ሂደቱ እንዲሳተፉ እናበረታታለን። እባክዎትን በዲኤችሲኤ ኮቪድ-19 ድረገጽ ላይ ያለውን መረጃ ይመልከቱ።